# ጋዜጣዊ መግለጫ

አሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ
2014/06

ለተጨማሪ መረጃ በ011-130-7033 ይደውሉ
ድረ-ገጽ - http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ እና የኢትዮጵያ መንግሥታት 1.6 ሚሊዮን ቤተሰቦችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የከተማ ጤና መርሃግብር ይፋ አደረጉ

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ የካቲት 04 ቀን 2006 ዓ.ም.፣** በዛሬው ዕለት የአሜሪካ መንግሥት በዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲው (ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ) አማካኝነት ከኢትዮጵያ ፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በኢትዮጵያ የከተማ ጤናን ማጠናከር የሚያስችል መርሃግብር ይፋ አደረገ፡፡ መርሃግብሩ ከፍተኛ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት በመስጠት በ49 ከተሞች ለሚገኙ ከ1.6 ሚሊዮን ለሚበልጡ ቤተሰቦች የተሻለ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

ይህ መርሃግብር ከዚህ ቀደም በዩ ኤስ ኤ አይ ዲ እና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል በኤች አይቪ፣ ቲቢ እና በእናቶች እና ሕጻናት ጤና ዘርፍ የተጀመረውን አጋርነት ያጠናክራል፡፡ ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ በሚሰጠው የቴክኒክ ድጋፍ የኢትዮጵያ መንግሥት የቤተሰብ ጤናን እና የጤና አገልግሎቶችን ጥራት፣ በጤና ተቋማት መካከል የሚደረጉ የሪፈራል ግንኙነቶችን እንዲሁም የከተማ ንጽሕናን እና የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓትን ያሻሽላል፡፡

የመርሃግብሩን መጀመር አስመልክቶ ንግግር ያደረጉት የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዶ/ር ከሰተብርሃን አድማሱ ፤ "በመጪዎቹ አስርት ዓመታት በርካታ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውን በከተሞች እንደሚኖሩ ይገመታል፡፡ በመሆኑም እያደገ የሚመጣውን የከተማ ነዋሪ ለመድረስ አዳዲስ ማህበረሰብ-ተኮር ስርዓቶችን መዘርጋት በመሰረታዊ የጤና ክብካቤ ስርዓታችን ቅድሚያ ከምንሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በከተሞች የሚታዩ የጤና አገልግሎት ልዩነቶችን ለማጥበብ የሚያስችል አመራር ለመስጠት እና ከአጋሮች ጋር በቅርበት ለመስራት ቁርጠኛ ነው፡፡" ብለዋል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2011 የተደረገው የስነሕዝብ እና ጤና ጥናት እንደሚያመለክተው በከተሞች የሚኖሩ ሰዎች በገጠር ከሚኖሩት እጅግ ባነሰ የጤና ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ በከተሞች የሚታየው 4.2 በመቶ የኤች አይ ቪ ስርጭት በገጠር ከሚታየው በአምስት እጥፍ ይበልጣል፡፡ 50 በመቶ የሚሆኑ እናቶች የሚወልዱት በቤት ውስጥ ሲሆን፤ በሕይወት ከሚወለዱ 1,000 ሕጻናት መካከል 41 ያህሉ በጨቅላነታቸው ይሞታሉ፡፡ በርካታ ከተሜዎች ጤና፣ ትምሕርት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዲሁም በቂ የውሃ እና የምግብ አቅርቦት ለማግኘት ይቸገራሉ፡፡

በኢትዮጵያ የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ሚሽን ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር በበኩላቸው፤" በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ከኢትዮጵያ መንግሥት፣ ከግሉ ዘርፍ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር እና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመጠቀም ከ1.6 ሚሊዮን ለሚበልጡ የከተማ ቤተሰቦች ከፍተኛ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ለማድረስ ይሰራል፡፡" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በጆን ስኖው ኢንኮርፖሬትድ እና በከፊል በአሜሪካው ፕሬዚደንት አስቸኳይ የኤድስ ዕርዳታ ዕቅድ (ፔፕፋር) የ20 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት የአምስት ዓመት መርሃግብር፤ እ.ኤ.አ. ከ2009 እስከ 2013 በከተሞች የጤና አገልግሎትን  ለማስፋፋት በመንግሥት ለሚደረጉ ጥረቶች ድጋፍ ሲያደርግ የነበረው የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን መርሃግብር ቀጣይ አካል ነው፡፡

###